# የክፍል የተማሪ መጠን

የክፍል ተማሪ መጠን በአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች ቢያንስ በ ቨርጂኒያ የጥራት ደረጃዎች (SOQ) የተገለፀውን መስፈርት እንዲከተል ይደረጋል። ቦርዱ የአዲስ የትምህርት ቤት አደረጃጀት እና የፈጠራ ሁኔታ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚመደቡ ተማሪዎችን ቁጥር ይወስናል። የክፍል መጠን ከትምህርት አንፃር አግባብ የሆነ እና የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያሞላ መሆን አለበት።

የሱፐርኢንቴንደንት እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሊቀበል የሚችለውን የተማሪ መጠን የሚመለከት ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል በተቻለ መጠን የትምህርት ቤቶችና የእያንዳንዱን ክፍሎች የተማሪ መጠን ባለው የክፍል መጠን ገደብ ደረጃ ወይም ከዚያ ባነሰ ደረጃ እንዲሆን ለማድረግ ክፍሎች የአካላዊ አቀማመጥ ውስንነት ወይም የትምህርት ክፍል መጠን ገደብ በመቀየሩ በማጤን። በIHB-R ደንብ መሰረት በማድረግ የሱፐርኢንቴንደንት እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የክፍል መጥን ገደብ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል። ይህንንም በጀት በሚፀድቅበት ወቅት በቦርዱ በማጥናት በየዓመቱ በአንድ ክፍል የሚኖረውን የተማሪዎችን ቁጥር ይወስናል። የሱፐርኢንቴንደንት እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሊቀበል የሚችለውን የተማሪ መጠን ሊወስን ይችላል።

የአንደኛ ደረጃ የአቅም ችሎታ በተለያዮ ሁኔታዎች አንፃር ሊወሰን ይችላል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም፣ ተጨማሪ ልዮ ፕሮግራሞች እና የትምህርት ቤት ህንፃዎች አቀማመጥ ጭምር በመመለከት ።

በየክፍል ደረጃ ያሉ የክፍል ሃላፊ አስተማሪዎች ክፍሎች ብዛት በተመለከተ የሱፐርኢንቴንደንት ሃሳብ ሊቀርብ ይችላል እና በስፐሪንግ ወቅት በበጀት ማፅደቅ ሂደት ሊወሰን ይችላል። በየክፍል ደረጃ የሚኖሩ ክፍሎች መጠን በትምህርት ቤት ቦርዱ አነስተኛ የተማሪዎችን ቁጥር የመኖር ፍሎጎትን ያንፀባርቃል።

በየዓመቱ ኤፕሪል 1 ቀን የሱፐርኢንቴንደንት በመጪው ዓመት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በትምህርት ቤት ፣ በክፍል ደረጃ ተለይቶ ምን ይህል እንደሚገመት በይፋ ያሳውቃል። የሱፐርኢንቴንደንት አንድ ትምህርት ቤት መቀበል ከሚችለው ገደቡ በላይ የመፈጠር ሁኔታ እንዳያጋጥም አንድ የመቆጣጠሪያ አሰራር ያበጃል።

በማንኛውም የትምህርት ዓመት ከሴፕቴምበር 30 በኋላ ባሉ በማንኛውም ጊዜ የተማሪው ቁጥር በቨርጅኒያ የጥራት ደረጃዎች ከተወሰነ የክፍል መጠን የበለጠ ከሆነ የትምህር ቤት አስተዳደር ክልሉ የዚህ ሁኔታ ባለበት ክፍሎች ለሚመሩ እያንዳንዱ ተማሪ ወላጅ በSOQ ከተቀመጠው በላይ ክፍሉ ሲበልጥ በ10 ቀናት ውስጥ ያሳውቃል። ማስታወቂያው በSOQ ከተቀመጠው በላይ ለምን የክፍል መጠን ሊበልጥ እንደቻለ ምክንያቱንና በፖሊሲው መሰረት የክፍል መጠን ለመቀነስ የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ስለሚወስደው እርምጃ ይገልፃል።

| | |
|---|---|
| የፀደቀው፡ | ጃንዋሪ 9፣ 1997 |
| የተሻሻለው፤ | ጁን 1፣ 2006 |
| የተሻሻለው፤ | ማርች 11፣ 2010 |
| የተሻሻለው፤ | ሜይ 19፣ 2016 |
| የተሻሻለው፤ | ኦክቶበር 24፣ 2016 |

የሕግ ማጣቅሻ፤ የቨርጂኒያ ህግ 1950 እንደተሻሻለው § -253.132.

| | | |
|---|---|---|
| የቃላት መፍቻ፤ | IHB-R | ከትምህርት ክፍል መጠን የተመለከቱ ደንቦች |
| | JC/JCD | የተማሪ ምደባ |
| | JC-R/JCD-R | የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪ ምደባ አማራጮች የሚወስኑ ደንቦች |